Learning on TAP




# አጋዥ ቴክኖሎጂ

## ቁልፍ መልዕክቶች፦ የመስማት አጋዥ መሳሪያዎች

## ትምህርት 1፦ የመስማት እና የተለያዩ የመስሚያ ችግሮች

### መስማት ምንድን ነው?

መስማት ማለት ድምጾችን በአካባቢ ውስጥ የመለየት እና የመገንዘብ ችሎታ ነው። ጆሮዎች የድምጽ ንዝረቶችን ይሰበስባል ከዚያም ወደ አንጎል የሚላኩ የኤሌክትሪክ ምልክቶች ይቀይራቸዋል። እነዚህ ምልክቶች አንጎል ጋር ሲደርሱ፣ ድምጾችን እንሰማለን እና ልንለያቸው እንችላለን። ሁሉም የጆሮ ክፍሎች ጥሩ መስማት እንዲኖር በአግባቡ ስራቸውን ማከናወን አለባቸው። በመስማት ውስጥ ያሉ የተለያዩ የጆሮ ክፍሎች፦

| ክፍል | ሚና | ቁልፍ ነጥቦች | ምስል |
|---|---|---|---|
| ውጫዊ | ከአየር ድምጽ ይሰበስባል እና ወደ ጆሮ ቱቦ አቅጣጫ ይመራል። | ቢጫ ወይም ቡኒ ቀለም ያለው የጆሮ ኩክ በጆሮ ቱቦ ውስጥ ይመረታል። የጆሮ ኩክ ጆሮን ለመጠበቅ እና ቆሻሻን ለማጽዳት ያግዛል። ኩኩ በተለምዶ በራሱ በጆሮ ትቦ በኩል ያልፋል። |  |
| መካከለኛው ክፍል | ድምጽ ጮክ እንዲል ያደርጋል። | የጆሮ ትቦ ወደ ጆሮ ታምቡር (tympanic membrane) ይመራል። የጆሮ ታምቡር የጆሮ ቱቦ እና ውስጠኛውን ጆሮ ይለያል። |  |
| ውስጣዊ ክፍል | ድምጾች ወደ ኤሌክትሪክ ምልክቶች ይቀይራል። | ውስጣዊ የጆሮ ክፍል ከሁለት ክፍሎች የተሰራ ነው።<br>• ኮክሊያ፦ የመስማት ስራን ይሰራል<br>• የሰውነት ሚዛን መጠበቅ (Vestibular) ሥርዓት፦ ወደ አንጎል መረጃን ይሰጣል ይህም ሚዛንን ለመጠበቅ ይረዳል። |  |

### የመስማት ችግር ምንድን ነው?

የመስማት ችግር ማለት በጤናማ የመስማት ደረጃ መስማት መቸገር ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ያለ ሰው ጸጥታ በሰፈነባቸው እና ጫጫታ ባለባቸው አካባቢዎች ውይይቶች ማድረግ አስቸጋሪ ሊሆንበት ይችላል። የመስማት ችግር ከመለስተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ሊደርስ ይችላል።

- **መለስተኛ፣ መካከለኛ** ወይም **ከባድ** የመስማት ችግር ያለባቸው ሰዎች ውይይቶችን ለመከታተል ችግር ይገጥማቸዋል። ይህ 'ለመስማት መቸገር' ተብሎ ይጠቀሳል።
- በሁለቱም ጆሮዎች **ከባድ** ወይም **ከፍተኛ** የመስማት ችግር ያለባቸው ሰዎች መስማት የተሳናቸው ናቸው።

መስማት የተሳናቸው ሰዎች የበለጠ ውስብስብ ፍላጎቶች አሏቸው እና ☞ ለጆሮ እና ለመስሚያ ባለሙያ መላክ /ሪፈር መደረግ አለባቸው።

የመስማት ችግር እንደ መደበኛ ምክንያቶች የሚያካትቱት፦

- ከመወለድ በፊት፣ በመወለድ ሰዓት ወይም ልክ እንደተወለዱ የሚከሰቱ ችግሮች
- የጆሮ በሽታዎች፣ በኩፍኝ፣ ጆሮ ደግፍ፣ ማጅራት ገትር ወይም የጆሮ ኢንፌክሽን የሚመጡ ኢንፌክሽኖች
- ባዕድ ነገሮች ወይም የተደፈኑ የጆሮ ኩክ የመሰሉ የጆሮ ችግሮች
- በዕድሜ መግፋት የሚመጣ የመስማት ችግር
- በጫጫታ አካባቢዎች የሚመጣ የመስማት ጉዳት

- በመድኃኒቶች ወይም ኬሚካሎች የሚመጣ የመስማት ጉዳት።

የመስማት ችግር ሰዎችን በተለያዩ መንገዶች ተጽዕኖ ያደርስባቸዋል። ህጻናት እና ልጆች የመስማት እና የመናገር ቋንቋ ክህሎቶችን ማጎልበት እንዲችሉ ንግግር ለመስማት ያስፈልጋቸዋል። የመስማት ችግር ያለባቸው ግለሰቦች በቤት፣ በስራ ቦታ፣ በት/ቤት እና ከጓደኞች ጋር ውይይቶችን ለማድረግ ችግሮች ሊገጥማቸው ይችላል። በልጆች እና በአዋቂዎች ላይ ቀድሞውኑ የመስማት ችግርን መለየት አስፈላጊ ነገር ነው።

### ጤናማ ጆሮዎች

የአንድ ግለሰብን የጆሮ ጤና ሲፈትሹ፣ በሁለቱም ጎኖች ያሉ የውጪ እና የውስጥ ጆሮዎቻቸውን መመልከት አስፈላጊ ነገር ነው። ሁልጊዜ የአንድ ግለሰብን ጆሮ ከፊት እና ከኋላ ሁልጊዜ ይፈትሹ። ጤናማ ጆሮ ሊኖረው የሚገባ፦

- ያልተደፈነ የጆሮ ቱቦ
- የጆሮ ታምቡር፦
  - በግልጽ ይታያል (በከፊል ወደውስጥ እንደሚታየው)
  - ነጭ/ነጣ ያለ የግራጫ ቀለም አለው
- ምንም የጉዳት ወይም የኢንፌክሽን ምልክት የሌለበት።

የግለሰቡ ፒና ወይም የጆሮ ቱቦ ከጎደለ ወይም በጣም የተለየ ቅርጽ ካለው፣ ግለሰቡ የበለጠ ውስብስብ ፍላጎቶች ይኖሩታል ስለዚህ ወደ ጆሮ እና የመስማት ባለሙያ ☞ ሪፈር መደረግ አለበት።

### የጆሮ ችግሮች

የጆሮ ችግሮች የግለሰቡን የመስማት ችሎታ ሊጎዱ ይችላሉ። ይሁን እንጂ፣ በርካታ የጆሮ ችግር ያለባቸው ሰዎች ሕክምና ሊያገኙ እና የመስማት ችሎታቸው ሊሻሻል ወይም ሙሉ ለሙሉ ወደቀድሞው ሊመለስ ይችላል። ለአንድ ግለሰብ የመስሚያ አጋዥ መሳሪያ ከማቅረብዎ በፊት ሁልጊዜ ያሉትን የጆሮ ችግሮች ይፈትሹ።

የጆሮ ችግሮች ያሉበት ግለሰብ ሊያጋጥሙት የሚችሉት፦

- ህመም
- የመስማት ችሎታ ማጣት
- ከጆሮ ውስጥ የሚወጣ ፈሳሽ።

**ማስጠንቀቂያ!** ሕክምና ያላገኙ የጆሮ ኢንፌክሽኖች የግለሰቡ የጆሮ ታምቡር እንዲበሳ ሊያደርጉ ይችላሉ

ሊከሰቱ የሚችሉ የመስማት ችሎታ ማጣት ችግሮች ከተወገዱ በኋላ፣ ግለሰቡ ዳግም በትክክል መስማት እንደሚችል ሊሰማው ይችላል። ግለሰቡ ጤናማ ጆሮዎች እንዳለው ሁልጊዜ ያረጋግጡ እና የመስማት ደረጃቸውን ለመመዘን የመስማት ምርመራን ማድረግዎን ይቀጥሉ።

## ትምህርት 2፦ የመስማት አጋዥ መሳሪያዎች

የመስማት አጋዥ መሳሪያዎች ለመስማት በሚቸገሩ በሁሉም የእድሜ ክልል ውስጥ ባሉ ሰዎች ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

### የተካተቱ የመስሚያ አጋዥ መሳሪያዎች

አንዳንድ በተለምዶ ጥቅም ላይ የሚውሉ የመስማት አጋዥ መሳሪያዎች ተካትተዋል፦

- **የመስሚያ መርጃዎች** በጆሮ ላይ የሚደረጉ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች ናቸው። ግለሰቡ የተሻለ መስማት እንዲችል አንዳንድ ድምጾች ጮክ ብለው እንዲሰሙት በማድረግ ያግዙታል። ቀድመው ፕሮግራም የተደረጉ እና ፕሮግራም የሚደረጉ የመስሚያ መርጃዎች ተካትተዋል።
- **ግላዊ የርቀት ማይክሮፎን ስርዓቶች** ጫጫታ በበዛባቸው ቦታዎች ውስጥ በተሻለ ለመስማት የመስሚያ መርጃዎችን ለሚጠቀሙ ሰዎች እገዛ ያደርጋል።

### ያልተካተቱ የመስሚያ አጋዥ መሳሪያዎች

የሚከተሉት መሳሪያዎች አልተካተቱም፦

- ጆሮ ውስጥ የሚገቡ የመስሚያ መርጃዎች
- ኮክሊያር ኢምፕላንቶች
- የማንቂያ ምልክት ሰጪዎች
- የዑደት ድግግም(Loop) ስርዓቶች
- የድምጽ መስክ ስርዓቶች።

## ትምህርት 3፦ የጆሮ ጤና ምርመራን እንዴት ማከናወን እንደሚቻል

የTAP የጆሮ ጤና ምርመራ አንድ ልጅ ወይም አዋቂ የጆሮ ችግር እንዳለበት እና/ወይም ለመስማት እንደሚቸገር ለማወቅ የሚደረግ ቀላል ሂደት ነው። አንድ ግለሰብ ከሚከተሉት ነገሮች ጥቅም ያገኝ እንደሆነ ለመለየት ይረዳል፦

- በደረቅ ጥጥ ማጽዳት ወይም ጆሮን ማጠብ
- የመስማት ምርመራ
- ሪፈራል ለጆሮ እና የመስማት ባለሙያዎች
- ሪፈራል ለሌሎች አጋዥ መሳሪያዎች።

ከመጀመርዎ በፊት፣ በታውን እና መሳሪያውን ያዘጋጁ። የጆሮ ጤና ምርመራውን ለግለሰቡ ያብራሩ እና ጆሯቸውን ለመመርመር ፈቃዳቸውን ይጠይቁ።

### የምርመራ ጥያቄዎች

ግለሰቡን ከመስማት ችግሮች እና የመስማት አጋዥ መሳሪያዎች ጋር ያላቸውን ተሞክሮ ለመረዳት ጥያቄዎችን ይጠይቁ።

አንዳንድ ሰዎች ውስብስብ ፍላጎቶች ካሏቸው እና ☞ ለተጨማሪ ምርመራ እና/ወይም ለሕክምና ወደ ጆሮ እና የመስማት ባለሙያዎች ሪፈራል ይፈልጋሉ። እነዚህ ውስብስብ ፍላጎቶች ተከታዮቹን ያካትታሉ፦

- እድሜያቸው ከአምስት አመት በታች የሆኑ ልጆች
- ለመናገር የማይችሉ ወይም ለመናገር የሚቸገሩ አዋቂዎች እና እድሜያቸው ከአምስት አመት በላይ የሆኑ ልጆች
- ተደጋጋሚ የጆሮ ፈሳሽ ያጋጠማቸው ሰዎች
- በአጭር ጊዜ ውስጥ (ባለፉት ሶስት ወራት) ድንገተኛ የሆነ የመስማት ለውጦች።

ግለሰቡ የመስማት አጋዥ መሳሪያን እየተጠቀመ ከሆነ እና አሁን ያለው መሳሪያ ላይ ችግር ካለበት፣ በፈቃዳቸው ☞ አጋዥ ምርትኡን በፍላጎት ወደተቀበለበተ አገልግሎት በታ ይላኩት/ሪፈር ያድርጉ።

### የጆሮ ጤና ምርመራ

የጆሮ ጤና ፍተሻን ለማከናወን፦

| ደረጃ | እርምጃ የጆሮ ችግር ከሆነ | እርምጃ የጆሮ ችግር ካልሆነ |
|---|---|---|
| 1. ከግለሰቡ ጆሮ (በእያንዳንዱ ጎን ፊት እና ኋላ) ውጪ ያለውን አካባቢ ይፈትሹ | • የሚከተሉት ምልክቶች ካሉ፦<br>◦ **ጉዳት፣ ኢንፌክሽን** ወይም<br>◦ የጆሮ ቱቦ **አለመኖር/የጆሮ/የጆሮ ቱቦ በጣም የተለየ ቅርጽ** ☞ ወደ ጆሮ እና የመስማት ባለሙያ ሪፈር ያድርጉ።<br>• አንድ ግለሰብ **ጉዳት ወይም ኢንፌክሽን** ካለበት ⟶ ሕክምና ካገኘ በኋላ ወደ ጆሮ ጤና ምርመራ እንዲመለስ ይጠይቁ።<br>• **የጆሮ ፈሳሽ** ምልክቶች ካሉ ⟶ የግለሰቡን ጆሮ በደረቅ ጥጥ ይጥረጉ። | **የጆሮው ውጪኛ ክፍል ጤናማ ከሆነ** ⟶ ይቀጥሉ። ወደ ግለሰቡ ጆሮ ይመልከቱ። |

| | | |
|---|---|---|
| 2. በኦቶስኮፕ (በእያንዳንዱ ጆሮ) የግለሰቡን ጆሮ ወደውስጥ ይመልከቱ | • **የኢንፌክሽን** ምልክቶች ካሉ ☞ ወደ ጆሮ እና የመስማት ባለሙያ ሪፈር ያደርጉ። አንድ ግለሰብ ሕክምና ካገኙ በኋላ ወደ ጆሮ ጤና ምርመራ እንዲመለስ ይጠይቁ።<br>• **የኢንፌክሽን** ምልክቶች ካሉ ☞ ወደ ጆሮ እና የመስማት ባለሙያ ሪፈር ያድርጉ።<br>• **የጆሮ ቱቦ በጆሮ ኩክ ከተደፈነ ወይም ባዕድ ነገር ውስጡ ካለ ⟶** የጆሮ እጥበት ያከናውኑ። እጥበቱን ከማከናወን በፊት፣ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ሁልጊዜ ያረጋግጡ። | **የውስጠኛው ጆሮ ጤናማ ከሆነ** ⟶ የመስማት ምርመራ ለማድረግ ያቅዱ። |
| 3. ካስፈለገ፣ የጆሮ አጠባ ያከናውኑ | • የጆሮ አጠባው ካልተሳካ ☞ ወደ ጆሮ እና የመስማት ባለሙያን ሪፈር ያድርጉ እና ሕክምና ካገኘ በኋላ ለጆሮ ጤና ምርመራ እንዲመለስ ያሳውቁ። | የጆሮ አጠባው **ስኬታማ** እና ጆሮ ጤነኛ ከሆነ ⟶ የመስማት ምርመራ ለማድረግ ያቅዱ። |

ሁለቱም ጆሮዎች ጤናማ ከሆኑ (ውጪው እና ውስጡ) አንድ ግለሰብ ከመስማት አጋዥ መሳሪያዎች ጥቅም ማግኘት ይችል እንደሆነ ለማረጋገጥ የመስማት ምርመራ ያድርጉ።

## ኦቶስኮፕ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

- ስፔኩለሙ በኦቶስኮፑ ላይ ማያያዣ ነው። ይህ በግለሰቡ የጆሮ ቱቦ ውስጥ ይገባል። ስፔኩለሙን ከመጠቀምዎ በፊት በጥጥ እና በጸረ-ተህዋሲያን ኬሚካል ያጽዱ።
- የግለሰቡን የቀኝ ጆሮ እየመረመሩ ከሆነ ኦቶስኮፑን በቀኝ እጅዎ ይያዙ እንዲሁም የግለሰቡን የግራ ጆሮ እየመረመሩ ከሆነ በግራ እጅዎ ይያዙት።

## የውስጥ ጆሮን እንዴት መመርመር ይቻላል

1. የጆሮ ምርመራ ከማድረግዎ በፊት እና በኋላ እጆችዎን በሳሙና ይታጠቡ እና ያድርቁት።
2. ትራገስን በቀስታ በመጫን ህመም እንዳለው ይፈትሹ። የህመም ምልክት ካለ፣ ኦቶስኮፕ መጠቀምዎን ያስወግዱ ወይም በጣም በቀስታ ይጠቀሙት
3. ፍሳሽ እንዳለ ይመርመሩ። በደረቅ ጥጥ በመጥረግ ፍሳሹን ያስወግዱ
4. ፒናን ወደላይ እና ወደኋላ በማድረግ በቀስታ በመሳብ የግለሰቡን የጆሮ ቱቦ ቀጥ ለማድረግ ጆሮን ያዘጋጁ። ታዳጊ ልጅ ከሆነ ፒናን በቀጥታ ወደኋላ ይሳቡ። በኦቶስኮፒ ጊዜ ፒና እንደያዙ ይቆዩ
5. ህመም ወይም ጉዳት ከማድረስ ለመቆጠብ ሁልጊዜ ኦቶስኮፕ በቀስታ ያስገቡ። ስፔኩለሙን በጣም ወደ ውስጥ ከማስገባት ይቆጠቡ። አንድ ግለሰብ ህመም ከተሰማው፣ ምርመራውን ያቁሙ
6. የጆሮ ታምቡሩን መመልከት ካልቻሉ፣ የጆሮ ኩክ እይታን እየዘጋ ወይም ኦቶስኮፑ በትክክል ያልተቀመጠ ሊሆን ይችላል። በቀስታ የኦቶስኮፑን አቀማመጥ ወደላይ እና ወደፊት ያስተካክሉ (ወደ ግለሰቡ አይኖች)
7. ሁልጊዜ ሁለቱንም ጆሮዎች ይፈትሹ!

## በደረቅ ጥጥ ጆሮ መጥረግ

ይህ ከግለሰቡ ጆሮዎች ውስጥ ፍሳሽን የማስወገጃ ደህንነቱ የተጠበቀ መንገድ ነው፡-

1. በደረቅ ጥጥ ጆሮ ከመጥረግዎት በፊት እና በኋላ እጆችዎን በሳሙና ይታጠቡ እና ያድርቁት።
2. “ሾል ያለ ለስላሳ ጨርቅ” ለማዘጋጀት ለስላሳ ጨርቅ ይጠቅእሙ
3. ለአዋቂ ፒናን ወደላይ እና ወደኋላ በቀስታ ይሳቡ ወይም ለልጅ ቀጥ አድርገው ይሳቡ
4. በቀስታ ወደ ግለሰቡ የጆሮ ቱቦዎች ሾል ያለ የሶፍት ጥቅልልን ከ2 እስከ 3 ሴንቲሜትሮች በማስገባት ያሽከርክሩ
5. በቦታው ላይ ለ10 ሰከንዶች ይተውት
6. የሾለውን የሶፍት ጥቅልል ያውጡ እና መግል ወይም ፈሳሽ ነገር እንደያዘ ይመልከቱ
7. የተጠቀሙበትን ሹል የለስላሳ ጨርቅ ጥቅልል ይጣሉ። ጥቅም ላይ የዋሉ የጆሮ የለስላሳ ጨርቅ ጥቅልሎችን ሲጥሉ የአካባቢ ደህንነት መመሪያዎችን ይከተሉ

8. ሌላ የለስላሳ ጨርቅ ጥቅልሎችን ወስደው ድጋሚ ያድርጉ። የለስላሳ ጨርቅ ጥቅልሉ እርጥብ መሆኑን እስከሚያቆምበት ድረስ መደጋገምዎን ይቀጥሉ
9. ሁሉም ፈሳሽ መወገዱን ለማረጋገጥ በኦቶስኮፑ የግለሰቡ ጆሮ ውስጥ ይመልከቱ።

### የጆሮ እጥበት

ይህ ጥቅም ላይ የሚውለው ከግለሰቡ የጆሮ ቱቦ የጆሮ ኩክ ወይም ባዕድ ነገር ለማጽዳት ነው።

**ማስጠንቀቂያ!** ግለሰቡ የሚከተሉት ሁኔታዎች ካሉት የጆሮ እጥበት መከናወን **የለበትም፦**

- የቅርብ ጊዜ የጆሮ ቀዶ ጥገና
- በጆሮ ታምቡር ውስጥ የሚታወቅ ነባር ቀዳዳ
- የጆሮ ኢንፌክሽን
- የጆሮ ሕመም።

ከላይ ካሉት ሁኔታዎች ለየትኛውም ችግር ካለ ☞ ግለሰቡን ወደ ጆሮ እና የመስማት ባለሙያ ሪፈር ያድርጉ።

የጆሮ እጥበትን ለማከናወን፦

1. የጆሮ እጥበት ከማድረግዎ በፊት እና በኋላ እጆችዎን በሳሙና ይታጠቡ እና ያድርቁት።
2. የውሃ ሙቀትን ይፈትሹ። ውሃው ሞቅ ያለ እንጂ ትኩስ ወይም ቀዝቃዛ መሆን የለበትም። 20 ሚሊሊትር ስሪንጅን በውሃ ይሙሉ
3. የኪድኒ ሳህን ወይም ሌሎች ጎድጓዳ ሳህኖችን በሰውየው ጆሮ ስር እንዲይዝ እና በአንገቱ ቆዳ ላይ አጥብቆ እንዲይዘው ይጠይቁት።
4. የስሪንጁን ጫፍ ወደ ግለሰቡ የጆሮ ቱቦ ያድርጉ
5. ሥስሪንጁ ወደጆሮ ቱቦው ጫፍ እና በትንሹ ወደኋላ እንዲሆን ያድርጉ።
6. ውሃውን ወደ ግለሰቡ የጆሮ ቱቦ ለመግፋት ስሪንጁን ይጫኑ
7. ውሃው ወደ ጎድጓዳ ሳህኑ ይፈስሳል እና የጆሮ ኩክ ወይም ባዕድ ነገር ሊይዝ ይችላል
8. የግለሰቡን ጆሮ በኦቶስኮፕ ዳግም ይመርምሩ
9. አስፈላጊ ከሆነ የተደፈኑ የጆሮ ቱቦዎችን ለማጽዳት የጆሮ እጥበትን ይድገሙ
10. ከእያንዳንዱ የጆሮ እጥበት በኋላ የግለሰቡን ጆሮ ይፈትሹ።

**ማስጠንቀቂያ!** ግለሰቡ የጆሮ ህመም ካጋጠመው የጆሮ እጥበትን ያቁሙ።

ከሶስት ሙከራዎች በኋላ የግለሰቡ ጆሮ አሁንም ከተደፈነ፣ በሚቀጥለው ቀን እንዲመለስ ይጠይቁ እና የጆሮ እጥበቱን ይድገሙ። ከሁለት ጉብኝቶች በኋላ የጆሮ ኩኩ ካልተወገደ፣ በግለሰቡ ፈቃድ☞ የጆሮ እና የመስሚያ ባለሙያ ጋር ሪፈር ያድርጉ።

## ትምህርት 4፦ እቅድ

### ሌሎች አጋዥ መሳሪያዎች

በጆሮ ጤና ምርመራ ጊዜ፣ ግለሰቡ በሌሎች አካባቢዎች ውስጥ አስቸጋሪ ነገሮች እንዳጋጠሟቸው ይጠይቁ። ለምሳሌ፣ የዕይታ፣ የእንቅስቃሴ፣ ራስን የመንከባከብ፣ የተግባቦት ወይም የእውቀት (ማሰብ እና/ወይም ማስታወስ)።

### ቀጣይ እርምጃዎች

- **ምርመራ ያድርጉ፦** ግለሰቡ በሌላ አካባቢ ውስጥ እክሎች ካሉባቸው፣ ለሌላ ችግር ምርመራ ማድረግ ይፈልጉ እንደሆነ ይጠይቋቸው።
- **ምዘና ያድርጉ፦** ግለሰቡ ጤነኛ ጆሮዎች ካሏቸው፣ የመስማት ምርመራ እንዲያደርጉ ያቅዱ።
- **ማስተላለፍ፦** ሪፈራሎችን ማድረግ ከግለሰቡ ጋር ሁልጊዜ ውይይት ሊደረግበት እና ስምምነት ላይ ሊደረስ ይገባል።
- **ክትትል ማድረግ፦** ግለሰቡ የጆሮ ኢንፌክሽኖች ህክምና ካደረገ በኋላ ጆሮውን ዳግም ለመመርመር የክትትል ቀጠሮ ማድረግ ያስፈልጋል። ከህክምና በኋላ የጆሮ ጤናው የተሻለ ካልሆነ፣ ☞ የጆሮ እና የመስማት ባለሙያ ጋር ሪፈር ያድርጓቸው።